 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ

**መግቢያ**

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሰው በአንድ የህዝብ ኩባንያ ውስጥ ያለውን የባለቤትነት ድርሻ የሚያረጋግጥ ብቸኛው ማስረጃ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት መያዝ ሲሆን ባለአክሲዮኑ ይህንን ወረቀት በደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ ይጠበቅበታል። የአክስዮኖችን ድርሻን በምስክር ወረቀት መልኩ መያዝ በርካታ ችግሮች የነበሩት ሲሆን የወረቀቱ መጥፋት፣ መበላሸት፣ መሰረቅ ፣ግብይቶች ጊዜ ወሳጅና ውድ መሆን፣ የባለቤትነት ክርክሮች መከሰት፣ የሐሰተኛ ወረቀቶች መፈጠር፣ በውርስ ጊዜ ረጅም የሕግ ሂደት መከተል፣እንዲሁም የአክሲዮን ዋጋ መለዋወጥን በቀላሉ መከታተል አለመቻል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እነዚህንና መሰል ችግሮችን በመቅረፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በዲጂታል ሥርዓት ለመገበያየት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 1248/2013 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ‹‹ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ መመሪያ ቁጥር1047/2017››ን አውጥቷል። ይህ መመሪያ ከዚህ ቀደም በወረቀት መልክ ይደረግ የነበረውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አያያዝ እና ግብይት ወደ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት የሚያሸጋግር ነው፡

ይህ እርምጃ የኢትዮጵያን የካፒታል ገበያ ሰነዶች ግብይት የሚያሳልጥ ከመሆኑ ባሻገር ግብይቱን የሚያዘምን፣ የኢንቨስተሮችን ጥቅም የሚያስጠብቅ እንዲሁም ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ ነው። መመሪያው ሁሉም ለሕዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ከወረቀት ፎርም አያያዝ እና ግብይት ወደ ኤሌክትሮኒክ ፎርም አያያዝ እና ግብይት እንዲሸጋገሩ (ግዑዝ አልባ እንዲደረጉ) ያዛል።ይህን የምዝገባ እና ሌሎች ከግብይት ጋር ተያያዥ የክፍያ ማጣራት፣ ርክብክብ እና መሰል ስራዎችን የሚያከናውነው በአዋጁ መሰረት ለዚሁ አላማ ተብሎ የተቋቋመው የማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ሲሆን ይህ ሥርዓት የባለቤትነት ዝውውርን ፈጣን እና ደህንነቱ የተጠበቀ ያደርገዋል።

በተጨማሪም ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ባለቤትነት በተያዙ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች እና በህዝብ ኩባንያዎች እንዲሁም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቻቸውን በፈቃዳቸው ግዑዝ አልባ ለማድረግ በሚወስኑ በግሉ ዘርፍ በተቋቋሙ አክሲዮን ማህበራት ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።

## ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ ማድረግ እና ሂደቱ

በአዋጁ የትርጓሜ ክፍል እንደ ተገለጸው ግዑዝ-አልባ ማድረግ ማለት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ማውጣት እና መመዝገብ ማለት ነው። ግዑዝ-አልባ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማለት ደግሞ የሰነደ ባለቤትነት በኤሌክትሮኒክ የምዝገባ ደብተር ባለቤትነትን በማስገባት ብቻ የሚረጋገጥለት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው።

የሰነዶችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ (Dematerialization) ባጭሩ በወረቀት ላይ የተመሠረቱ ሰነዶች የባለቤትነት ማረጋገጫ ሆነው የሚያገለግሉበት ጊዜ የሚያበቃበትና እና በምትኩ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት (Central Securities Depository) ውስጥ የኤሌክትሮኒክ መዝገብ ላይ የመመዝገብሂደት ነው።

በመሆኑም በመመሪያው መሰረት ለሕዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችወይም መመሪያው ከመውጣቱ በፊት ለህዝብ የተሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ-አልባ መደረግ አለባቸው። እነዚህ ሰነዶች እንዴ ግዑዝ-አልባ ከሆኑ በኋላ ሕጋዊ ተቀባይነት ያላው

 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ

ባለቤትነት ማረጋገጫ ከመሆን ባሻገር፣ ትክክለኛ የገንዘብ ዋጋ ያላቸው ሰነዶች እንደሆኑ ይቆጠራሉ። ግዑዝ-አልባ የተደረጉ ሰነዶች የባለቤትነት ዝውውርም የሚደረገው በዚሁ ኤሌክትሮኒክ መዝገብ አማካኝነት ብቻ ይሆናል።

በመመሪያው መሠረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ የማድረግ ሂደት በርካታ ደረጃዎችን ያካትታል።

በመጀመሪያ ደረጃ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች ለሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዠች (ባለቤቶች) በመመሪያው ውስጥ ስለተካተቱ መስፈርቶች፣ግዑዝ-አልባ የማድረግ ሂደትን እና ሂደቱንም እንዲጀምሩ ማሳወቅ አለባቸው።፤ በተጠየቁ ጊዜም የሂደቱን ሁኔታ እና ያለበትንደረጃ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

ስለ ሂደቱም ማስታወቂያ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ከማሳተም በተጨማሪ በስልክ መልዕክት፣ በኢሜይል ወይም በሌላ መገናኛ መስመር ለባለ አክሲዮኖቻቸው እና ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ አለባቸው።

## ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ማስመዝገብ

ለሕዝብ ሽያጭ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ-አልባ ከመደረጋቸው በተጨማሪ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት መመዝገብ አለባቸው። ይህ ግምጃ ቤት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን የሚመዘግብ እና ግብይት ሲፈጸም የዝውውር ሂደቱን በሂሣብ መዝገብ ውስጥ ብቻ እንዲከናወን የሚያደርግ ሥርዓት ነው። በዚህ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚያዘው የኤሌክትሮኒክ መዝገብ የባለ አክሲዮኖችን መለያ ዝርዝሮች፣ በየሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ያዥ የወጡ እና የተያዙ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መጠን፣ሰነዱ በብድር የተያዘም ከሆነ ግብይት የማይካሄድበት መሆኑን ማመላከት እና በሕግ የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን በመመዝገብ ሕጋዊ የባለቤትነት መረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

## የአክስዮን ባለቤቶችን መረጃ ወደ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ማከማቻ ግምጃ ቤት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪ ሂሳብ ማዘዋወር እና ማስታረቅ

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አውጪዎች የአክሲዮን ባለቤቶችን መረጃ ወደ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ከማዛዋወራቸው በፊት በርካታ ቅድመ ዝግጅቶችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ ለሁሉም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዠች ትክክለኛ የመገኛ አድራሻቸውን እንዲሞሉ ያስታውቃሉ። ከዚያም አውጪዎች ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ ግዑዝ-አልባ እንዲደረግ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ መዝገቡን ከማቅረባቸው አስቀድመው የሁሉንም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዠችን እና ያላቸውን የባለቤትነት ጥቅም ዝርዝር ማስታረቅ ይጀምራሉ። ይህ የማስታረቅ ሥራ የወጡ ሰነዶች ብዛት እና የሚወከሉት ካፒታል መጠን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዠች ስም፣ የመገኛ አድራሻ ዝርዝር፣ ልዩ መለያ፣ በመቶኛ ያለውን መጠን እንዲሁም በመያዣነት ለተያዙ ሰነዶች የመያዣ ሰጪ እና ተቀባይ መረጃ ማካተት አለበት።

በመቀጠልም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ አውጪዎች መረጃውን በሚመዘገቡበት ቅጽ መሠረት ሁሉንም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዠች መዝገብ ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት እንዲገቡ ያቀርባሉ። የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጩ በቅጹ ላይ የተሞላውን መረጃ ትክክለኛነት፣የመዝገቡን ዝግጁነት እና በባለሥልጣኑ ሰነደ ሙዓለ ንዋዩ መመዝገቡን ካረጋገጠ በኋላ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹን በማዕከላዊ ግምጃ ቤቱ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዡ ስም ተከፍቶ በአውጪው በሚተዳደር ሂሣብ ውስጥ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል። በዚህ ሂደት ውስጥ አውጪው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ጊዜያዊ ተወካይ ጠባቂ ሆኖ ይሠራል። በመጨረሻም የአውጪው የወረቀት ሰነድ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት ምዝገባ በሙሉ በማዕከላዊ ግምጃ ቤቱ በኤሌክትሮኒክ መልኩ በሚያዘው ዘመናዊ ሥርዓት ይተካል። ከዚህ በኋላ ማንኛውም የአክሲዮን ግብይት ወይም የባለቤትነት ሽግግር የሚከናወነው በዚህ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ብቻ ይሆናል።

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal

 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ

## የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሣብ መክፈትና የምስክር ወረቀቶችን ተቀማጭ ማድረግ

ማንኛውም ኢንቨስተር የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሣብ ለመክፈት የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል። ኢንቨስተሩ በመጀመሪያ ደረጃ በባለሥልጣኑ ፈቃድ ካገኙ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ አባላት (Depository Members) አንዱን መምረጥ አለበት። በካፒታል ገበያ አዋጅ መሰረት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪ ፈፃሚ ኩባንያ አባል ወይም በመመሪያ መሰረት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭ ተብሎ የተጠቀሰው የካፒታል ገበያ ተሳታፊ፣ ባንክ፣ በተውሶ ስም የሚሰራ፣ ወይም ሌላ የፋይናንስ ተቋም ሆኖ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግብይት ክፍያ ለማጣራትና ለመፈጸም የሚያስችል፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚቀበልበት፣ የሚይዝበት እና የሚያስተላልፍበት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሂሳብ መዝገብ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ወይም በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ያለው ነው።

እነዚህ አስቀማጭ አባላት የራሳቸውን ሀብት ከደንበኞቻቸው ሀብት ለይተው የማስቀመጥ ግዴታ አለባቸው። ኢንቨስተሩ ለአስቀማጭ አባሉ ተቀባይነት ያለው የማንነት መግለጫ ማቅረብ እንዲሁም የደንበኛህን ዕወቅ (KYC) መስፈርት ማሟላት ይጠበቅበታል።

በመቀጠልም ኢንቨስተሩ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አስቀማጭአባሉ ያዘጋጀውን የሂሣብ መክፈቻ ቅጽ በትክክል ሞልቶ ቅጹን እና አስፈላጊ ሰነዶችን ለአስቀማጭ አባሉ ያቀርባል፣ አስቀማጭ አባሉ መረጃውን ተቀብሎ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል። የአስቀማጭ አባሉ ማረጋገጫ ካገኘ በኋላ፣ በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ላይ በኢንቨስተሩ ስም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሣብ ይከፍታል።

ሂሣብ ከተከፈተ በኋላ፣ ኢንቨስተሩ ግዑዝነት ያላቸውን የምስክር ወረቀቶች ወይም ሌላ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ለአስቀማጭ አባሉ ያስረክባል፣አስቀማጭ አባሉም የተረከበውን ሰነድ ለአውጪው ይልካል፤ አውጪውም ትክክለኛነታቸውን እና ከራሱ መዝገብ ጋር መስማማታቸውን ካረጋገጠ በኋላ፣ ሰነዶቹ በኢንቨስተሩ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ሂሣብ ውስጥ ገቢ ይደረጋሉ። በመጨረሻም፣ አውጪው የምስክር ወረቀቶቹ ግዑዝ-አልባ መደረጋቸውን የሚገልጽ ምልክት በማድረግ መረጃዎቹንም ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ጠብቆ ማቆየት አለበት። ከዚህ በኋላ ኢንቨስተሩ የኤሌክትሮኒክ ሂሣቡን በመጠቀም አክሲዮኖቹን መግዛት፣ መሸጥ ወይም ማስተላለፍ ይችላል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

## በዋስትና የተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ-አልባ ማድረግ

በዋስትና የተያዙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችም ግዑዝ-አልባ ለማድረግ ልዩ ሂደትን የሚጠይቁ ሲሆን አውጪያቸው ምዝገባውን በሚያስገባበት ወቅት የመያዣውን ዝርዝር ማቅረብ ይኖርበታል።

እነዚህ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዡ ሂሣብ ውስጥ ገቢ ከመደረጋቸው በፊት መያዣ ተቀባዩ ከመያዣ ሰጪው ጋር መመካከር ያለበት ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ሰነዶቹን ግዑዝ-አልባ ለማድረግ መተባበር ይጠበቅባቸዋል።

ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ አንዴ ገቢ ከተደረጉ በኋላ፣ በማዕከላዊ ግምጃ ቤቱ ሂሣብ ውስጥ በዋስትና የተያዙ መሆናቸውን የሚገልጽ ምልክት ይደረግባቸዋል።

 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# ለህዝብ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ

## በሙሉ እና በከፊል ክፍያ የተፈጸመባቸው አክሲዮኖችን ግዑዝ-አልባ ማድረግ

ሙሉ በሙሉ ክፍያ የተፈጸመባቸው አክሲዮኖች ግዑዝ-አልባ መደረግ እና በማዕከላዊ ግምጃ ቤት ሂሣብ ውስጥ ገቢ መደረግ አለባቸው። በዋስትና የተያዙ፣ሕጋዊ ገደብ የተጣለባቸው ወይም በተፈቀደ የተውሶ ስም የተያዙ ካልሆኑ በስተቀር ግዑዝ-አልባ የተደረጉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምንም ዓይነት የግብይት ክልከላ ሊደረግባቸው አይገባም። ነገር ግን ያልተከፈሉ ወይም በከፊል የተከፈሉ አክሲዮኖች ግዑዝ-አልባ ሊደረጉ የሚችሉት ሙሉ ለሙሉ ክፍያ ከተፈጸመባቸው በኋላ ብቻ ነው። በዚህ ረገድ መመሪያው አክሲዮኖችን ወደ ኤሌክትሮኒክ ሥርዓት ከማስገባት በፊት ክፍያቸው መሟላቱን ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

## ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ-አልባ ከማድረግ ጋር የሚነሱ ስህተቶች እና ቅሬታዎች

መመሪያው ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግዑዝ-አልባ በሚደረጉበት ጊዜ የተለያዩ ስህተቶች ቢከሰቱ በምን አይነት አካሄድ ሊታረሙ እንደሚገባ ይደነግጋል። በዚህ መሰረት የሚፈጠሩ ማንኛውም አይነት ስህተቶች፣ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች በመጀመሪያ ደረጃ ለአውጪው በጽሁፍ መቅረብ አለባቸው። አውጪውም ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ባሉት በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ስህተቱን እንደ አግባብነቱ መፍታት ወይም ማስተካከል ይጠበቅበታል። አውጪው ቅሬታውን ለመፍታት በቅሬታ አቅራቢው የቀረበውን መረጃ፣ የራሱን የውስጥ መዝገብ፣ እንዲሁም ግዑዝነት ያለውን ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጨምሮ ሌሎች ማናቸውንም ምንጮች በመጠቀም በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ስህተቱን እንደ አግባብነቱ ፈቶ የተሰጠው ውሳኔ የማዕከላዊ ግምጃ ቤት መዝገብ ወይም መረጃ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ፣መረጃው እንዲስተካከል ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት በሁለት የሥራ ቀናት እንዲሁም የቅሬታውን ወይም የስህተቱን የመጨረሻ ውሳኔ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

ነገር ግን ቅሬታው በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ካልተፈታ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በአውጪው በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ከሆነ፣የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ያዡ አውጪው በሰጠው ውሳኔ ላይ ለካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

ለባለሥልጣኑ የሚቀርበው በቅሬታው የነበረውን ጠቅለል ያለ ሒደት እና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ቅጂን መያዝ ይኖርበታል። ባለሥልጣኑ የቀረበውን ቅሬታ እና አጠቃላይ መረጃ ተመልክቶ በአሥር የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤ በባለሥልጣኑ ውሳኔም ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተገለጸለት በኋላ ባሉት በሃያ ስምንት የሥራ ቀናት ውስጥ ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኙን ማቅረብ በአዋጅ የተሰጠው መብት ነው። ይህ አጠቃላይ ሂደት ቅሬታዎች በፍጥነት እንዲፈቱ እና የኢንቨስተሮች መብት እንዲጠበቅ ያስችላል።